# በ ‹አኬልዳማ› ዶክመንተሪ ፊልም ዙሪያ ብዙዎች ብዙ ቢሉም ያልተነካውን ነገር ልነካ እኔም ቀለሜን ከወረቀቱ ላይ አገናኘሁ፡፡

(ፍኖተ ነፃነት 2ኛ ዓመት ቅፅ 2 ቁጥር 20 ታህሳስ 03 2004 ገፅ 4)

የዘመኑ ኢህአዴግ የፖለቲካ ፍልስፍና ውስጥ ብቸኛው ደራሲ አቶ መለስ ናቸው፡፡ በእሳቸው ቃለ ተውኔት ላይ ሂስ የሚሰነዝር ደፋር ከቶ አልተገኘም፡፡ እሳቸው ይደርሳሉ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያዘጋጃል፡፡ ምናልባት ወደፊት ስልጣን አንገሽግሾአቸው ቢለቁ ፊልም ለመስራት ወደ ሆሊውድ ቢያቀኑ ሳያዋጣቸው አይቀርም፡፡ ምን ይታወቃል? የኦስካር ተሸላሚም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህስ አንቀናባቸውም፡፡ እሳቸው ያደርግላቸውን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ለይ ብቻ ይውረዱ እንጂ፡፡

የሰሞኑ «አኬልዳማ» በሽብርተኝነት ላይ ተጠርጥረው በታሰሩት ላይ ፍርድ ቤትን ተክቶ ለመፍረስ ያነጣጠረ ነው፡፡ በተለይም አንዱዓለም አራጌን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን፣ ዓምደና ርዕዮት አለሙን... ለመወንጀል ለመድረክ የበቃ የአቶ መለስ ስርዓት ድርሰት ነው፡፡

አዘጋጅቶ ያሳየን ኤቲቪም የዚሁ ስርዓት አካል ነው፡፡ ጋዜጠኞቹ እንደሆኑ እንደበታቸው ለውሸት የተባ በሬ ወለደን የሚዘግቡ ናቸው፡፡ «አኬልዳማ»ን ለእይታ ለማብቃት የምስል ላይብረሪያቸውን አድሰው በ1984 ዓ.ም ኦነግ ፈፅመው የተባለውን (ፍርዱን ለታሪክ ትተነው) ጭፍጨፋ 20 ዓመታትን ወደኋላ አስጋልቦ ሊያሳየን መሞከሩ አስገራሚ ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ዝባዝንኬ ኢትዮጵያ የአሸባሪዎች ስብሰባ መሆኗን «ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሀል!» እንዳሉ ሆኖ እንጂ አቶ መለስና ኢቲቪ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች በመሆናቸው የደራሲውና የአዘጋጁ ጉዳይ ብዙም አያስገርምም፡፡ ላለፉት 20 ዓመታት ማንነታቸውን ስለምናውቅ፡፡

ብዕሬን ያስነሳኝ ግን የደበበ እሸቱ ተውኔት ነው የ«አኬልዳማ» ተውኔት መሪ ተዋናይ በእርግጥም ደበበን ሆኖ የወጣ ይመስላል፡፡ እንደ አስተኔ ገፀባህርያት በአንድ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ብቅ ቢልም ክፍል አንድና ሁለት የክፍል ሶስት ትዕይንት ማጀቢያ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ አርቲስት ደበበም በተውኔት አለም መድረክ ላይ የሚያሳየውን ስብዕና (ለማሳቅም በመሞከርም) መተወኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅስም የሰበረና ይሁዳ ክርስቶስን አሳልፎ እንደሰጠው እነ ርዕዮት አለሙን አሳልፎ ለመስጠት የማይለውን አለ፡፡ በ1997 ዓ.ም ቅንጅትን በመወከል ከኢትዮጵያ ምድር ባሻገር አሜሪካና አውሮፓ እየዞረ ሲቀሰቅስ የነበረው ደበበ እሸቱ በስተርጅና ቀባሪ አጣ፡፡ ከኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ውልቅ ብሎ ወጣ፡፡ ኧረ ይች አገር ምን ይበጃት? ሰው እንዳታፈራ ተረገመች? ያ ከ40 ዓመታት በላይ በኪነ-ጥበብ መድረክ ላይ አንቱ የተሰኘው ደበበ ምናለበት ከነክብሩ መቃብር ቢወርድ? ሞት እንደሁ አይቀር፡፡ ሰው በሰባ እና በሰማንያ ዓመቱ የወጣትነት ዘመን ሀጢያቱ እንዲሰረይለት ወደ እግዚአብሄር ተግቶ እንደሚፀልይ የአባቶቻችን ታሪክ ያስተምረናል፣ ከአቶ መለስም በላይ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩት ላይ የፈረደው ደበበ እሸቱ እንደሆነ ኢትዮጵያውያን ልብ ልንል ይገባል፡፡

ሌላኛው ማስተዋል የሚገባን ጉዳይ ኢህአዴግ አስቀድሞ ደበበን ያሰረው ለአላማ ነው፡፡ እነ አንዱአለም አራጌን ከወጥመዱ ለማስገባት ደበበ እሸቱን መጠቀም ግድ ይለዋል፡፡ በሽብርተኝነት ተፈርጀው ቃሊቲ የወረዱትን ትንታግ ወጣቶች የትግል ወኔያቸውን ለመስለብና ወጣት ተከታዮቻቸውን ለማስፈራራት በዚህ ፍሬ ፈርሰኪ ተውኔት ውስጥ ደበበ እሸቱ የግንቦት 7 ድርጅት መልማይ ሆኖ መተወን ግን ለኢህአዴግ ውሃ የሚያነሳ ማስረጃ ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነውና ኢትዮጵያ ውስጥ የዜጎች በህግ ፊት እኩል አለመሆንን ፍንትው አድርጎ የሚያሳየን ሰዎችን ለግንቦት ሰባት አባልነት ሲመለምል የነበረው ደበበ እሸቱ ከእስር ተለቅቆ በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ወንጀለኛ አለመሆናቸውን የሚናገሩት መታሰራቸው ነው፡፡ ደበበ እሸቱ ከእስር ተለቅቆ በፍርድ ቤት ከርክር ላይ ወንጀለኛ አለመሆናቸውን የሚናገሩት መታሰራቸው ነው ደበበ እሸቱ በሽብርተኝነት ለተፈረጀው ግንቦት ሰባት አባላትን መመልመሉና የድርጅቱን ፅሁፎች በሚስጥር መበተኑን በ80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ፊት በመወትወቱ (ያውም ማስፈራራትና ዛቻ ሳይደርስበት ትኩስ ቡናውን እየላፈ) በራሱ ላይ መስክሯልና በፀረ ሽብር ህጉ መሰረት ዘብጥያ መውረድ ነበረበት፡፡ ከዕድሜውና እስከ ዛሬ ከተወነባቸው የተውኔት ስራዎቹ አንፃር ደበበ እሸቱ ለተተኪው ትውልድ አርአያ መሆን የማይችልና ለአመታት የገነባውን ስብእና በሰአታት ውስጥ የናደ አሳፋሪ ፍጡር ነው፡፡

እ/ር ለሁላችንም ልቦና ይስጠን!!